የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን
ETHIOPIAN CAPITAL MARKET AUTHORITY

**For Immediate Release**
Date, October 1, 2025
Ethiopian Capital Market Authority
Addis Ababa, Ethiopia

# Ethiopian Capital Market Authority (ECMA) Grants Licenses to Three New Capital Market Service Providers

The Ethiopian Capital Market Authority (ECMA) is proud to announce the granting of licenses to three (3) new capital market service providers (CMSPs) after a rigorous license application review process. The licensing event took place on Wednesday, 01 October 2025, at the ECMA's Head Office, increasing the total number of licensed CMSPs from eight to eleven.

The new licensees and their license categories are:

1. **First Addis Investment Bank PLC** - Investment Bank
2. **Ignite Capital PLC** – Securities Investment Advisor
3. **Zuri Capital S.C** - Securities Investment Advisor

During the event, the Director General of the ECMA, Hana Tehelku, extended her congratulations to the newly licensed service providers. She underscored the importance of their role in advancing Ethiopia's capital market, encouraging them to contribute actively to the development of an inclusive, transparent, and resilient financial system.

The Ethiopian Capital Market Authority once again extends its congratulations to the three newly licensed service providers and reaffirms its commitment to a strong, inclusive, and resilient capital market in Ethiopia.

## About ECMA

The Ethiopian Capital Market Authority (ECMA) stands as a pivotal institution mandated to foster the development and regulation of the capital market within the Federal Democratic Republic of Ethiopia.

Established under Article 3(1) of the Proclamation, the ECMA operates as an independent regulatory body with its own juridical identity, reporting directly to the Prime Minister of Ethiopia. Embracing a multifaceted approach, the ECMA is committed to enhancing investor confidence, facilitating capital mobilization, and promoting sustainable economic growth through robust regulatory frameworks and strategic initiatives.

**For more information, please visit *ecma.gov.et.***

## For enquiries & additional information contact

**Contact:** Communications & Public Relations Directorate
**Phone:** 011-5-57-81-62
**Email:** communication@ecma.gov.et

የኢትዮጵያ የካፒታል
ገበያ ባለሥልጣን

ETHIOPIAN CAPITAL
MARKET AUTHORITY

# ጋዜጣዊ መግለጫ

**መስከረም 21//2018 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ**

## የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣን ለሦስት አዲስ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጭዎች ፈቃድ ሰጠ

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን ከሰፊ የፈቃድ ማመልከቻ ግምገማ ሂደት በኋላ ለሦስት (3) አዳዲስ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጭዎች ፍቃድ በመስጠቱ የተሰማውን ደስታ ይገልጻል።

ፈቃድ የተሰጣቸው አገልግሎት ሰጭዎች መስከረም 21/2017 ዓ.ም በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን ዋና መስሪያ ቤት  በተዘጋጀ መርሃ ግብር ከባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ሀና ተኸልቁ የፈቃድ ምስክር ወረቀቶታቸውን የተቀበሉ ሲሆን በዚህም በባለስልጣኑ ፈቃድ የተሰጣቸው የካፒታል ገበያ  አገልግሎት ሰጭዎች  ቁጥር ከስምንት ወደ አስራ አንድ ከፍ ብሏል።

አዳዲሶቹ ፈቃድ የተሰጣቸው አገልግሎት ሰጭዎች እና እና የፈቃድ አይነቶችም የሚከተሉት ናቸው፣

1. **ፈርስት አዲስ ኢንቨስትመንት ባንክ ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር** - በኢንቨስትመንት ባንክ ዘርፍ፣
2. **ኢግናይት ካፒታል ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር** - በሰነደ ሙዓለንዋይ ማማከር ዘርፍ፣
3. **ዙሪ ካፒታል አክሲዮን ማህበር** - በሰነደ ሙዓለንዋይ ማማከር ዘርፍ፣

በፈቃድ አሰጣጥ መርሃ ግብሩ ላይ የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ሀና ተኸልቁ በእለቱ ፈቃድ ለተሰጣቸው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጭዎች የእንኳን ደስ አላችሁ መልዕክት ያስተላለፉ ሲሆን ሀገራችን በጀመረችው አካታች እና ሁሉን አቀፍ የካፒታል ገበያ ስርዓት ግንባታ ላይም ወሳኝ ሚና እንዲጫወቱ አሳስበዋል።

በዛሬው እለት ፈቃድ ከተሰጣቸው ሶስቱ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጭዎች መካከል ፈርስት አዲስ ኢንቨስትመንት ባንክ ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ከባንክ ግሩፕ ውጭ ፈቃድ የተሰጠው የመጀመሪያው ኢንቨስትመንት ባንክ ሆኗል።

ከዚህ በተጨማሪም የኢግናይት ካፒታል ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና የዙሪ ካፒታል አክሲዮን ማህበር ፍቃድ ማግኘትም በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ስነ-ምህዳር ብቃት ያላቸው የሰነደ ሙአለ ንዋይ አማካሪ ድርጅቶች ቁጥር እያደገ መምጣቱን እና በካፒታል ገበያው ላይ እየጨመረ የመጣውን እምነት ማሳያ ነው።

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን በሀገራችን ጠንካራ እና አካታች የካፒታል ገበያ ስርዓት እንዲገነባ ያለውን ቁርጠኝነት እየገለጸ አዲስ ፈቃድ ለተሰጣቸው ሶስቱ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጭዎች በድጋሚ እንኳን ደስ አላችሁ ለማለት ይወዳል።


**ለጥያቄዎችና ተጨማሪ መረጃ**

**የኮሙኒኬሽን እና የህዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት**

**ስልክ:** 011-5-57-81-62

**ኢሜይል:** communication@ecma.gov.et